የወ/መ/ቁጥር 159454

የልደታ ምድብ 1 ኛ ወንጀል ችሎት

ሐምሌ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ ወ/ሮ የመንዝወርቅ ዘማርያም ይፍረዴ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ነሐሴ 27 ቀን 2001 ዓ.ም በተሻፈ የክስ አቤቱታ ተከሳሽ በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 675(1) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ጥር 03 ቀን 2001 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 2፣30 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07 ልዩ ቦታው መድኃኒያለም ቤተክርስቲያን አካባቢ የግል ተበዳይ ብዛታቸው 50 የሆኑ ሴቶች በችግር ጊዜ ብለው ያቋቋሙትን የቡና ዕድር እና የሴት እድር እንድትይዝ የተሰጣትን ብር 3311.00(ሦስት ሺህ ሦስት መቶ አስራ አንድ) ብር ለራሷ ጥቅም በማዋል በፈፀመችው የእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሳለች በማለት ክስ ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሷትና ተነቦላት ከተረዳችው በኋላ ክሱን ሳትቃወምኀ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብላ ክዳ በመከራከሯ ዐ/ሕግ ሦስት ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን በሰጡት ምስክርነትም ተከሳሽን ጨምሮ ያለንበት ሁለት የሴቶች እድር ነበረን፤ ተከሳሽ የእድሩ ገንዘብ ያዥ ስትሆነ በኋላ ግን በክሱ ላይ በተመለከተው ቀን ተከሳሽ ገንዘቡን እንድታመጣ ስትጠየቅ ለመመለስ አልቻለችም፤ የገንዘቡ መጠንም በክሱ ላይ የተገለፀው መሆኑን ያስረዱ ሲሆን ፍ/ቤቱም የእድሩን መዝገብ አስቀርቦ እንደተመለከተው በርካታ የእድር አባለት እንዳሉ፤ ተከሳሽም የእድሩ ገንዘብ ያዥ መሆኗን አረጋግጧል። በዚህም መሰረት ተከሳሽ በክሱ ላይ የተመለከተውን ድርጊት መፈፀሟን ዐ/ሕግ ባቀረበው ማስረጃ ያረጋገጠ ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 675(1) ስር እንድትከላከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዛለች።

ተከሳሽም እከላከላለሁ ብላ አንድ የመከላከያ ምስክር በማቅረብ ያሰማች ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነት ያስመዘገበችው ገንዘቡ መጥፋቱን፤ የገንዘብ ማስቀመጫው ሳጥን ቁልፍም ጠፍቶ አብረን ሆነን የሰበርነው መሆኑን፤ በሳጥኑ ውስጥ የነበረ ወርቅ ጭምርም መጥፋቱን አስረዳለሁ የሚለውን ሲሆን በዚሁ መሰረትም የመከላከያ ምስክሯ ቀርባ እንደ እምነቷ መኃላ ፈፅማ የመሰከረች ሲሆን ቃሏም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ ባቀረበችው የመከላከያ ምስክር ቃል በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባትን ክስና ማስረጃ አስተባብላለች ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን በተከሳሽ በኩል የቀረበችው የመከላከያ ምስክር ተከሳሽ

የእድሩን ገንዘብ ያስቀመጠችበት ሳጥን ቁልፍ ጠፍቶ አብረን ሆነን የሳጥኑን ቁልፍ በመስበር ስንከፍተው ገንዘቡም ሆነ የግራቀኛችን የወርቅ ጌጥ የጠፋ መሆኑን አረጋግጠናል በማለት አስረድታለች። ይሁን እንጅ ተከሳሽ በወቅቱ ገንዘብ የተቀመጠበት ቁልፍ ሲጠፋ እንኳ ለሚመለከተው የፖሊስ አካል አለማመልከቷ ጠፍቷል የሚለው አቤቱታ ጥርጣሬ ውስጥ የሚወድቅና ተአማኒነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል። ምክንያቱም በመጀመሪያ ደረጃ ቁልፉ ጠፍቶ እስከ አንድ ሳምንት የሚቆይበት ሁኔታ የለም። ከዚህ ሌላ ተከሳሽ የራሷ ንብረት ብቻ ሳይሆን የእድር ገንዘብን ያህል ንብረት ጠፍቶ እንዲሁ ቁጭ ትላለች ተብሎ የሚገመት አይደለም። በመሆኑም ተከሳሽ በእምነት በአደራ የተቀበለችውን ገንዘብ ለግል ጥቅሟ አላዋለችውም የሚለውን ግምት የሚያስተባብል ማስረጃ ያላቀረበች ስለሆነ እንድትከላከል በተባለችበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 675(1) ስር ጥፋተኛ ናት በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ ፍ/ቤቱ ደረጃውን ሲወስን ከባድ በማለት እንዲወስነው፤ ምክንያቱም በዝቅተኛ ገቢ የሚኖሩ ነዋሪዎች ያጠራቀሙትን ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ ስለሆነ ነው በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 42 ዓመት ነው፤ የትምህርት ደረጃዬ 4 ኛ ክፍል ነው፤ ትዳርና ልጅ የለኝም፤ ነገር የእህቴ ሁለት ልጆች (የ 23 እና 18 ዓመት የሆናቸው) ከእኔ ጋር ይኖራሉ፤ ቤት በማከራየት ነበር የምተዳደረው ነገር ግን አሁን ቤቱ በክርክር ምክንያት ለቅቄ ከዘመድ ጋር ተጠግቼ ነው የምኖረው፤ ከገንዘቡ ውስጥ እስከ አሁን ድረስ ብር 400.00(አራት መቶ ብር) ከፍያለሁ በማለት አመለከተች።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል

እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሹ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 675(1) /የእምነት ማጉደል ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

የወንጀል ሕግ አንቀፅ 675(1) እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን ፍ/ቤቱ በቅድሚያ ከሁለቱ የቅጣት አይነቶች የትኛውን እንደሚቀጣ መወሰን ስላለበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 106 እና 108 ላይ ከተገለፀው ድንጋጌዎች አንፃር አሁን የተፈፀመው ወንጀል ለሕብረተሰቡ እጅግ አደገኛ ነው የማይባል ስለሆነ ተከሳሽን በፅኑ እስራት ከመቅጣት በቀላል እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመበት የንብረት መጠን ብር 3311.00(ሦስት ሺህ ሦስት መቶ አስራ አንድ ብር) ስለሆነ ይህ ደግሞ ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን ስለሆነ የወንጀሉ ደረጃም ዝቅተኛ ነው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 675(1) ለወንጀሉ የተቀመጠው መነሻና መድረሻ ከአስር ቀን እስከ አንድ ሺህ ዘጠና አምስት ቀን ቀላል እስራት የቅጣት እርዝመት ለአራት ተከፍሎ ስሌቱን በመስራት የተገኘው ውጤት ደረጃ የሚለው የሚወድቀው ከአስር ቀን እስከ ሁለት መቶ ሰማንያ አንድ ቀን ባለው መካከል ስለሆነ በመመሪያው አንቀፅ 13(7) መሰረት አንድ መቶ ሃምሳ ቀን ወይም አምስት ወር መነሻ ቅጣት ተብሎ ተወስኗል።

ይህ በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት በአባሪ አንድ እርከን 3 ላይ የሚታይ ሲሆን ፍቅደ ስልጣኑም/range/ ከሁለት ወር እስከ አምስት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት ሦስት ወር ከአስራ አምስት ቀን እስራት ነው።

ከዚህ በመነሳት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ስላላቀረበ ፍ/ቤቱ የመነሻ ቅጣት እርከኑን ከፍ አላደረገውም። በሌላ በኩል ተከሳሽም የቅጣት

አስተያየት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 እና 86 መሰረት በማስረጃ የተደገፈ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ያላረቡ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የመነሻ ቅጣት እርከኑን ዝቅ አላደረገውም።

ስለሆነም ከላይ እንደተገለፀው ቅጣቱ በአባሪ አንድ እርከን 3 ላይ በተመለከተው ፍቅድ ስልጣን/range/ ማለትም ከሁለት ወር እስከ አምስት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ባለመኖሩ በሦስት ወር ከአስራ አምስት ቀን ቀላል እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ከዛሬ ጀምሮ በማሰብ የተወሰነው የእስራት ቅጣት እንዲያስፈፅም ታዟል።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

3 ኛ. በችሎት ቀርበው የነበሩት የእድር ደብተሮች ለአባለት ተወካይ ዛሬ በችሎት ተመልሶላቸዋል።

4 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

5 ኛ. ተከሳሽ ሐምሌ 12 ቀን 2002 ዓ.ም አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ ፍ/ቤት ቀጠሮ አለኝ ስላሉ ማ/ቤት በቀጠሮ ቀን እንዲያቀርባቸው ታዟል።

6 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።